በአስቸኳይ የሚለቀቅ

አድራሻ፡- Perry Cooper | የሲያትል ወደብ ከፍተኛ የሚዲያ ሃላፊ

(206) 787-4923 | cooper.p@portseattle.org

ለሳውዝ ኪንግ ካውንቲ ኢኮኖሚያዊ እድል $2.5 ሚሊየን በአዲስ ፈንድ መልክ ይገኛል

ማህበረሰብ-መር ቡድኖች እና ለትርፍ ያልተቋቋሙ ድርጅቶች አሁን በ Seattle-Tacoma International Airport (SEA፣ የሲያትል-ታኮማ አለም አቀፍ አየር መንገድ) ዙሪያ ባሉ ከተሞች ኢኮኖሚያዊ እድሎችን ለመጨመር ለሲያትል ወደብ ፈንድ ማመልከት ይችላሉ። የሳውዝ ኪንግ ካውንቲ የማህበረሰብ ተጽዕኖ ፈንድ (SKCCIF) የኢኮኖሚ ማገገሚያ ፕሮግራም አራተኛ ዙር ሲጀመር በጠቅላላው $2.5 ሚልየን ይኖራል።

ድርጅቶች ለአንድ አመት እስከ $100,000 ፈንድ ለማግኘት እና ለበርካታ አመታት እስከ $250,000 ፈንድ ለማግኘት ማመልከት ይችላሉ። የማመልከቻ ጊዜው ከአሁን ጀምሮ እስከ ጁላይ 21 2023 ድረስ ክፍት ነው።

እንዲሁም ወደቡ ዛሬ በ SKCCIF የኢኮኖሚ ማገገሚያ ፕሮግራም ሶስተኛ ዙር ውስጥ $1.3 ሚሊየን ፈንድ የሚያስገኙ ስድስት ድርጅቶችን አስተዋውቋል። የኢኮኖሚ ማገገሚያ ፕሮግራም በአቪየሽን፣ የባህር ሃይል፣ የግንባታ ንግድ እና የአረንጓዴ ሙያን ጨምሮ በወደብ ነክ ኢንዱስትሪዎች ውስጥ የቀጣዩ ትውልድ ባለሙያዎችን ስንመለምል ከፍተኛ ፍላጎት ያላቸውን የሳውዝ ኪንግ ካውንቲ ማህበረሰቦች ጥሩ ክፍያ ከሚከፍሉ የስራ እና ስልጠና እድሎች ጋር ያገናኛል።

“በርካታ ቤተሰቦች የኢኮኖሚ አለመረጋጋት እና ችግር እያጋጠማቸው ይገኛል - አሁንም ድረስ በ Covid-19 እየተቸገሩ ነው፣” **ሲሉ የሲያትል ወደብ ኮሚሽን ምክትል ፕሬዘዳንት Toshiko Grace Hasegawa ተናግረዋል።** ”ይህ የኢኮኖሚ ማገገሚያ ፕሮግራም የኢኮኖሚያዊ እድገት እድሎች ወደተለያዩ ማህበረሰቦች መድረሳቸውን ያረጋግጣል እንዲሁም በወደቡ ላሉ ሙያዎች እቅዶችን ያዘጋጃል።”

“በፍትሃዊ አጋርነቶች በኩል፣ ወደቡ በስርዓቱ ውስጥ ከእድሎች ለተገለሉ ማህበረሰቦች ኢኮኖሚያዊ እድሎችን ይፈጥራል።” **ሲሉ የሲያትል ወደብ ኮሚሽነር Hamdi Mohamed ገልጸዋል።** ”የሳውዝ ካውንቲ ማህበረሰብ ተጽዕኖ ፈንድ የኢኮኖሚ ማገገሚያ ፕሮግራም (South King County Community Impact Fund Economic Recovery Program) በእነዚህ ማህበረሰቦች ውስጥ ጥራት ያላቸው፣ ቤተሰብ ለመርዳት በቂ የሆነ ደመወዝ የሚያስገኙ ስራዎችን ይበልጥ ተደራሽ እንዲሆኑ ያደርጋል እናም በወደብ ነክ ኢንዱስትሪዎች ውስጥ የሚሳተፉ ሰራተኞችን ቁጥር ያሳድጋል።”

**ከወደብ ነክ ኢንዱስትሪዎች ጋር ግንኙነቶች**

ከሁሉም የዋሽንግተን ቁልፍ የኢኮኖሚ ዘርፎች ትስስር እና በእኛ ተቋም ውስጥ ከ 500 በላይ አሰሪዎች ጋር ባለው ግንኙነት፣ ወደቡ በወደብ ኦፕሬሽኖች ተጽዕኖ የደረሰባቸውን ማህበረሰቦችን የሚጠቅሙ ጥሩ ደመወዝ የሚያስገኙ እቅዶችን ለመፍጠር በልዩ ሁኔታ ተቀምጧል። በርካታ የወደብ ነክ ኢንዱስትሪዎች የሰራተኛ እጥረት እያጋጠማቸው ስለሆነ አሁን ላይ የሰራተኛ እድገት መዋዕለ ንዋዮች ልዩ ጠቀሜታ አላቸው። ማህበረሰብ-መር ፕሮጀክቶች ተሳታፊዎች ከጊዜ ወደ ጊዜ ውስብስብ እና ቤተሰብ ለመርዳት በቂ የሆነ ደመወዝ የሚያስገኙ ስራዎችን በወደብ እና ወደብ ነክ በሆኑ ኢንዱስትሪዎች ውስጥ እንዲያገኙ የሚያስፈልጋቸውን ክህሎቶች፣ ልምድ እና ትምህርት እንዲያገኙ ያግዛሉ።

የአንደኛ እና ሁለተኛ ዙር ፈንድ ተቀባይ Businesses Ending Slavery and Trafficking (BEST፣ ባርነትን እና ህገወጥ የሰዎች ዝውውርን የሚያስቆሙ የንግድ ስራዎች) በሳውዝ ኪንግ ካውንቲ ውስጥ የሚኖሩ ከሰዎች ዝውውር የተረፉ እና አደጋ ላይ ያሉ ታዳጊዎችን ያገለግላል። ድርጅቱ የስራ ቅጥር ዝግጁነት ስልጠና በማድረስ፣ በወደብ ነክ ኢንዱስትሪዎች ውስጥ ያሉ አሰሪዎችን በመደገፍ፣ እና ከህገወጥ የሰዎች ዝውውር የተረፉ እና በአየር መንገድ እና በወደብ ነክ ኢንዱስትሪዎች ውስጥ አደጋ ላይ ያሉ ታዳጊዎችን ደመወዝ የሚከፍሉ ስራዎችን እና የስራ እድሎችን በመፍጠር ኢኮኖሚያዊ እድልን ይደግፋል።

“ከህገወጥ የሰዎች ዝውውር የተረፉ መጀመሪያ አዘዋዋሪዎቻቸውን ሲተዉ፣ ደህንነት ቀዳሚው ነገር መሆን አለበት። ነገር ግን ከድንገተኛ መጠለያ ጋር ከተገናኙ እና መሰረታዊ ፍላጎቶቻቸው ከተሟሉላቸው በኋላ፣ የተረፉት ሰዎች ህይወታቸውን እንደገና መገንባት እንዲችሉ ለማገዝ ስራ ያስፈልጋቸዋል። **በማለት ለትርፍ ያልተቋቋሙ ባርነትን እና ህገወጥ የሰው ዝውውርን የሚያስቆሙ የንግድ ስራዎች (BEST)**

**ፕሮግራሞች ዳይሬክተር Hannah Farkas አብራርተዋል።** "የሲያትል ወደብ የሳውዝ ኪንግ ካውንቲ የማህበረሰብ ተጽዕኖ ፈንድ (Port of Seattle South King County Community Impact Fund) በወደብ ነክ ኢንዱስትሪዎች ውስጥ ከህገወጥ የሰዎች ዝውውር ለተረፉ ሰዎች የስራ እድሎችን የማቅረብ ችሎታችንን በሚገባ ያጠናክራል።"

የሁለተኛ ዙር ፈንድ ተቀባይ Latino Civic Alliance (የላቲኖች ሲቪክ አሊያንስ) እንዳሉት ከሆነ ድርጅቱ ከዚህ ቀደም የሰራተኛ እድገት እና የቅድመ-ልምምድ ፕሮግራም ላልነበራቸው ላቲኖች ግንዛቤን እንዲያስጨብጥ የወደብ ፈንድ አግዞታል።

"የወደብ ፈንድ ለኑሮ ተስማሚ የሆነን ደመወዝ እና የለማጅ ስራ ፕሮግራሞችን እውቀት፣ ዋጋ እና ጥቅሞች እና ይህ ቤተሰቦችን እንዴት ከድህነት እንደሚለውጥ ለማወቅ፣ ከታዳጊ አዋቂዎች እና ከቤተሰቦቻቸው ጋር በጋራ ለመስራት አስችሎናል" **ሲሉ የሃብት እድገት እና የ Latino Civic Alliance አስተዳደር ዳይሬክተር Marie Bravo ተናግረዋል።**

**የሶስተኛ ዙር ተቀባዮች**

እስከዛሬ ድረስ፣ 21 የሳውዝ ኪንግ ካውንቲ ድርጅቶች በ SKCCIF የኢኮኖሚ ማገገሚያ ፕሮግራም በመጀመሪያ፣ በሁለተኛ እና በሶስተኛ ዙሮች ፈንድ ተቀብለዋል።

Veronique Facchinelli፣ የሶስተኛ ዙር ፈንድ ተቀባይ የማህበረሰብ ፕሮግራም ዳይሬክተር፣ Casa Latina እንደተናገሩት፣ ፈንዱ እነሱ ለሚደግፏቸው ማህበረሰቦች ድርጅቱ ኢኮኖሚያዊ እድልን ለማሳደግ ስልጠና እና አገልግሎት ለመስጠት እንዲችል ያደርገዋል።

"ይህ ፈንድ ብዙ የ Latinx ስደተኛ ማህበረሰብ አባላት ለኑሮ ተስማሚ በሆነ ደመወዝ እና በወደብ ነክ ኢንዱስትሪዎች (የግንባታ ንግድ፣ አረንጓዴ ስራዎች እና ሌሎችም) ትላልቅ ስራዎችን እንዲያገኙ ያስችላል የሚል ተስፋ አለን።" ሲሉ Facchinelli ተናግረዋል። "ለዚህ ፈንድ ምስጋና ይሁን እና፣ Casa Latina የ Latinx ማህበረሰብን ከተገቢ ስልጠናዎች፣ ሪፈራሎች ጋር ሊያገናኟቸው ይችላሉ እንዲሁም ወደ ቅድመ-እና-ንግድ የስራ ልምምድ ፕሮግራሞች የተለያዩ መንገዶችን እንዲመለከቱ ይረዷቸዋል። ይህም ማህበረሰቡ በወደብ ነክ ስራዎች ለማመልከት በቂ ክህሎት እንዲያገኝ ያስችላል።"

በኢኮኖሚ ማገገሚያ ፕሮግራም ሶስተኛ ዙር አማካኝነት ፈንድ ስለሚያገኙ ቡድኖች እና ፕሮጀክቶቻቸው የበለጠ ይወቁ፡-

**የፓሲፊክ ኖርዝዌስት የአፍሪካ ንግድ ምክር ቤት (ACCPNW)**

ACCPNW's African Drayage Trucking Business Support Project (ADT-BUS፣ የ ACCPNW የአፍሪካ የወደብ ማጓጓዣ ንግድ የድጋፍ ፕሮጀክት) የመጓጓዣ ንግዳቸው እንዲተርፍ እና እንዲያድግ ለአሽከርካሪዎች የንግድ ቴክኒካል ድጋፍ ያደርጋል፤ ወደብ ተቋማትን የሚያገለግሉ የመጓጓዣ ስራ ፈጣሪዎች የራሳቸውን ንግድስኬታማ በሆነ መንገድ ማካሄድ እንዲችሉ ስለ አነስተኛ የቢዝነስ አስተዳደር ያስተምራል።

**BIPOC Apostrophe**

BIPOC Apostrophe እድሜያቸው ከ 18-25 የሆኑ ታዳጊዎችን በአውሮፕላን ካርጎ አስተዳደር፣ በሎጂስቲክስ ማዕከላት እና በመጋዘን ተግባራት፣ እና በአውሮፕላን ማርሻል ዘርፎች ላይ ያሰለጥናል።

**የኪንግ ካውንቲ ወንድ እና ሴት ልጆች**

የኪንግ ካውንቲ የወጣቶች ሃይል ፕሮግራምየወንዶች እና የሴቶች ልጆች ክለቦች፣ ከ7GEN እና SIXR ጋር በመተባበር በአየር መንገድ አቅራቢያ ከሚገኙ ማህበረሰቦች በኢኮኖሚ ደካማ የሆኑ ወጣቶችን በአረንጓዴ ቴክኖሎጂ እና የተሻሻለ የምርት ስልጠና ወደ ቅድመ-ስራ ልምምድ እና የልምምድ ስልጠና መንገዶችን ያገናኛል።

**Casa Latina**

የካሳ ላቲና የግንባታ ፕሮግራም የላቲኖ ሰራተኞች በኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ውስጥ ስራዎችን ለማግኘት የሚያስፈልጉ ክህሎቶችን እና ስልጠናዎችን በመመልመል፣ በማሰልጠን፣ እና በማረጋገጥ ላይ ነው። ይህ ፕሮግራም ወንዶችን፣ ሴቶችን፣ እና ጎልማሶችን ለመደገፍ የጉዳይ አስተዳደር እና የማጠቃለያ አገልግሎቶችን ያካትታል።

**Serve Ethiopians**

የServe Ethiopians አዲስ ጅማሬ ፕሮግራም ለስደተኛ BIPOC የጉዞ መጋራት እና የታክሲ ካብ አሽከርካሪዎች በ SEA የአየር መንገድ የአውሮፕላን መካኒክ ሙያ እንዲቀጥሉ እና በኤርፖርት ዩኒቨርሲቲው በሚቀርበው "የአቪዬሽን ጥገና ቴክኖሎጂ መግቢያ (AMT)" ኮርስ ላይ እንዲሳተፉ ያደርጋል።

**የእርስዎ ገንዘብ አማካሪ**

በኮንስትራክሽን ስልጠና ፕሮግራም መግቢያ የትምህርት እና የማማከር ድጋፍ በማድረግ በኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ውስጥ የስራ እድልን ለማረጋገጥ ተሳታፊዎች የግንባታ ክህሎቶች፣ ብቃቶች፣ ልምድ፣ እና ትምህርት ያገኛሉ። ተሳታፊዎች በ Abatement እና Demolition ሰርትፍኬት ያገኛሉ።

ወደቡ ለአንድ አመት ከ $100,000 እና በርካታ አመታት እስከ $250,000 ፈንድ ለማግኘት ለሚያመለክቱ አመልካቾች የብዙ አመት ሽልማቶችን መስጠቱን ይቀጥላል። የብዙ አመት ፈንድ ድርጅቶች በረጅም ጊዜ እቅድ እና ትግበራ ላይ መዋዕለ ንዋይ እንዲያፈሱ እና የወደብ ማህበረሰብ መዋዕለ ንዋዮችን ተጽዕኖ እንዲጨምሩ ያስችላቸዋል።

አስራ ሁለት ድርጅቶች በብዙ አመት ፈንድ በኢኮኖሚ ማገገሚያ ፕሮጀክቶች ላይ መስራታቸውን ቀጥለዋል። ሳውዝ ኪንግ ካውንቲ ማህበረሰብ ተጽዕኖ ፈንድ የኢኮኖሚ ማገገሚያ ፕሮግራም ገጽ ላይ የበለጠ ይወቁ። [https://www.portseattle.org/programs/south-king-county-community-impact-fund-economic-recovery-program](https://www.portseattle.org/programs/south-king-county-community-impact-fund-economic-recovery-program)

**የዙር 4 ማመልከቻ ሂደት**

ከሰራተኛ እድገት፣ የስራ ፈጠራ፣ ወይም በወደብ ነክ ኢንዱስትሪዎች ውስጥ ኢኮኖሚያዊ እድገት ጋር የተያያዘ ውጤት ያለው ፕሮጀክት አለዎት? ለኢኮኖሚ ማገገሚያ ፕሮግራም ፈንድ ያመልክቱ።

ለፈንድ ለማመልከት፣ የብቁነት ውሳኔን እስከ ጁላይ 21 2023 ባለው ጊዜ ያጠናቅቁ። በማመልከት ሂደት፣ በፕሮፖዛል ቁሳቁሶች እና ቀደም ሲል በተሸለሙ ፕሮጀክቶች ላይ ተጨማሪ መረጃ ያግኙ>

https://www.portseattle.org/programs/south-king-county-community-impact-fund-economic-recovery-program

**ቁልፍ ዝርዝሮች**

- ድርጅቶች ለሁለቱም ለአንድ እና ለብዙ አመት የፈንድ አማራጮች ማመልከት ይችላሉ።
- ፈንዱ ከስራ ሃይል እድገት፣ ከስራ ፈጠራ ፕሮግራሞች፣ ወይም ከወደብ ነክ ኢንዱስትሪዎች ውስጥ ከኢኮኖሚ ማገገሚያ ጋር ለሚያያዙ ፕሮጀክቶች ሃሳቦችን ያቀርባል።
- ፕሮጀክቶች ሳውዝ ኪንግ ካውንቲን የሚደግፉ መሆን አለባቸው።
- ፕሮጀክቶች ቀለም ያላቸውን ሰዎች፣ የሃገሩን ተወላጆችን፣ ስደተኞችን እና ጥገኞችን፣ የእንግሊዝኛ ተማሪዎችን፣ የበፊት ወታደሮችን፣ ታላላቆችን፣ ወጣቶችን፣ እና/ወይም አካል ጉዳተኞችን ጨምሮ በኢኮኖሚ ደካማ የሆኑትን ሰዎች ማገዝ መቻል አለባቸው።
- በእነዚህ የፕሮግራም ዘርፎች ውስጥ የሚሰሩ የማህበረሰብ ድርጅቶች፣ የንግድ ክፍሎች እና ሌሎችለትርፍ ያልተቋቋሙ ድርጅቶች ለማመልከት ብቁ ናቸው።
- የወደብ ሰራተኞች በማመልከቻው ሂደት ውስጥ አመልካቾችን ለመደገፍ የመረጃ ክፍለጊዜዎችን ያዘጋጃሉ።

**ስለ ሳውዝ ኪንግ ካውንቲ የማህበረሰብ ተጽእኖ ፈንድ**

ወደቡ የሳውዝ ኪንግ ካውንቲ ተጽእኖ ፈንድን በ2019 ያልተጠበቁ፣ የተለያዩ ጎሳዎች እና ባህሎች ያላቸውን ማህበረሰቦችን እድሎች ለመጨመር አቋቁሟል።SKCCIF ወደቡ ለፍትሃዊ ማገገም፣ አካባቢ ዘላቂነት እና ለጥሩ ጥራት ያለው ህይወት ያለውን ራዕይ ለማሳካት የሚሰራበት አንዱ መንገድ ነው።ፈንዱ በ2019 እና 2024 መካከል 10 ሚሊዮን ዶላር የሚሸልም ይሆናል። ከ2019 ጀምሮ ከ54 በላይ ፕሮጀክቶች የSKCCIF ፈንድ አግኝተዋል፣ ይህም ማህበረሰብ መር ፕሮጀክቶች ፍሬያማ እንዲሆኑ ረድቷል። ከእነዚህ ፕሮጀክቶች ውስጥ ብዙዎቹ ባልተጠበቁ እና እንግሊዝኛ በማይናገሩ ማህበረሰቦች ውስጥ የስራ ማመልከቻ ድጋፍ ጨምረዋል፣ ለቅድመ-ልምምድ

ፕሮግራሞች እና የባህር ውስጥ ሙያዎች መልምለዋል፣ የአትክልት ቦታዎችን ገንብተዋል፣ የጋራ ቦታዎችን አጽድተዋል እና የአካባቢያው እውቀትን አስፍተዋል።

ለኢኮኖሚክ ማገገሚያ ፈንዲንግ ዛሬ ያመልክቱ> https://www.portseattle.org/programs/south-king-county-community-impact-fund-economic-recovery-program